# በጭልጋ በኩል የተከፈተብን ጦርነት በብልፅግና ኦሮሞ እና ትህነግ የተቀናጀ ስምሪት ነው እስከ ማስረጃ ።

ጎብዝ በጭልጋ በኩል የተከፈተብን ጦርነት የተቀናጀ ነው።ይህን ውጊያ አንድ ሁነን መመከት ግድ ይለናል።የወቅቱን ተጨባጭ የጠላት አሰላለፍ በመረዳት ሁሌም እንደምለው የርዕዮተ-ዓለሙ ልዩነት ይቆየን።የፖለቲካ ልዩነታችንን ማስተናገድ የምንችለው አገርና ህዝብ ሰላም ሲሆን ነው።አገርና ህዝብ ሲኖረን ነው።አሁን አንገብጋቢው ህልውናችን ጉዳይ ነው።የህልውና ትግሉ ይቅደም እያልኩ ነው።

በጭልጋው ውጊያ ከአሸባሪው የቅማንት ኮሚቴ ጋር የተቀናጀ ጦርነት የከፈቱብን በሱዳንና በግብጽ ቅንጅት የሽብር ስልጠና ወሱደው ሰርገው የገቡት እኩዮች ናቸው።ከሽብርተኛው ቡድን መካከል በርካቶች ተደምስሰዋል።ከተደመሰሱት አሸባሪዎች ውስጥ ማንነታቸውን በጉልህ መለየት የሚያስችል መታወቂያ ተገኝቷል።ከቁስለኛው መካከልም የአሸባሪው ትህነግ ልዩ ኃይል/ትግሬዎች እና በኦሮሞ ብልጽግና ፓርቲ ባሉ አመራሮች የሚደገፈው የአሸባሪው የኦነግ ታጣቂዎች አብረው ተገኝቷል።ለዚህም ነው የተከፈተብን ጦርነት የተቀናጀ ነው እያልኩ ያለሁት።የጥምረት ነው።

ይደገም።ሰሞኑን በዋግህምራ (አበርገሌ) በኩልም ሽብርተኞቹ የሽብር ተግባር ለመፈጸም ሞክረዋል።ሙከራቸው ለአማራ ህዝብ የህይወት መስዋእትነት እየከፈለ በሚገኘው በጀግናው የአማራ ልዩ ኃይልና በዋግ ሹሞች አገር ህዝብ ተመክቷል።ድብቅ ተመትቷል።የቀረው ወደ ዋሻው ተመልሷል።ወደ ዋሻው የተመለሰው አሸባሪ ኃይል እንደ ገና አንሰራርቶ ለሽብር ተግባር መምጣቱ አይቀርም።ምክንያቱ ዓላማው ነውና።ስለሆነም በእየ አቅጣጫው አማራ በመሆናችን ብቻ የተከፈተብነን የሽብርና የጥፋት ተግባር መመከት የምንችለው ከብረት በጠነከረ አንድነት ነው።ከአለሎ በጠጠረ አድረጃጀት ነው።

በአጣዬ፣በከሚሴ... በኩል ያለው አሸባሪ አሁን ለጊዜው አሰበከ እንጂ አልተደመሰሰም።እንዲውም በኦሮሞ ብልጽግና አመራር የሚደገፈው ኦነግ ሸኔ በርካታ አዳዲስ አሸባሪዎችን ማስመረቁን እየነገረን ነው።

እናም ከግራም ከቀኝም፣ከውጭም ከውስጥም የተደቀነብነን ጥፋት ለመመከት ፍጹም አንድ የሆነ አደረጃጀት እንጂ ፖለቲካዊ ጎራ ለይቶ መጠዛጠዝ ያስፈልገናል ብዩ አላምንም።ፖለተካዊ ልዩነቱ ከህልውና ማኖር በኋላ ይደርሳልና!!

አምደማሪያም እዝራ